Montgomery County Public Schools
UNLEASHING POTENTIAL

# ፈጣን መመሪያ

## *የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ፀረ- ጥላቻ መድልዎ ፕሮቶኮል*

**እያንዳንዱ ተማሪ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ ደጋፊ፣ እና ምቹ የመማሪያ አካባቢ ይገባዋል።**

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ፀረ-ጥላቻ መድልዎ ፕሮቶኮል--እንድንገነዘብ ይረዳናል

- ክስተቶች እንዴት እንደሚስተናገዱ እና ለተጎዱ ሰዎች የሚሰጠውን ድጋፍ የሚያሳይ ባለ ሶስት እርከን ስርዓት/ሲስተም።
- ክስተቶች እንዴት እንደሚለዩ፣ እንደሚስተናገዱ፣ እና እንዴት የትምህርት ቤቶቻችን ማህበረሰብ እንዲያውቁት እንደሚደረግ።
- MCPS ውስጥ በማንኛውም መልኩ የሚደረግ መድልዎ ተቀባይነት የለውም።
- MCPS የተጠረጠሩ ጉዳዮችን ሲገመግም፣ ሁኔታውን ያነሳሳው ነገር ምን እንደሆነ እና የተከሰተውን አውድ በሙሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ።
- የትምህርት ቤት እና የቤተሰብ አጋርነት ወሳኝ በመሆኑ በማህበረሰቦቻችን ውስጥ በጥላቻ ምክንያት የሚፈፀም የአድልዎ ክስተቶችን ለማስቆም የጋራ ጥረት ማድረግን ይጠይቃል።

*የዚህ ስርዓት ዓላማ የሁሉንም ተማሪዎች እና ሰራተኞችን ደህንነት እና ሠላም ማረጋገጥ ነው።*

### MCPS ሁሉንም ክስተቶች ይመረምራል

MCPS የሚከተሉትን የጥላቻና አድልዎ ስሞታዎች በሙሉ ይመረምራል፡- a) በትምህርት ቤት ንብረት ላይ (ወይም በትምሕርት ቤት አውቶቡስ ላይ)፣ በትምህርት ቤት ድጋፍ የሚካሄድ እንቅስቃሴ ወይም ዝግጅት ላይ የሚከሰቱ ድርጊቶችን፣ ወይም b) የትምህርት ቤትን የመማር ማስተማር ሥርዓትና አሠራር በእጅጉ የሚያውኩ ከሆነ። ለምሳሌ፡- የጥላቻ ንግግር፤ የዘር መድልዎ፣ የጎሰኝነት ወይም ሌላ ስድብን፤ የጥላቻ ወይም የዘረኝነት ምልክቶችን፣ የተወገዙ ባንዲራዎችን ወይም ስዕሎችን ማሳየት፤ የአካል ጉዳተኝነትን መሳለቂያ ማድረግ፤ ወይም ስለ አንድ ሰው ማንነት አጸያፊ "ቀልዶችን" መናገርና ማሠራጨትን ያካትታል፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ የተወሰኑ አይደሉም።

### ባለ ሶስት እርከን ስርዓት

- ቢጫ ቀለም፡- **እውነታውን የማጣራት/የማረጋገጥ እርምጃዎች ተወስደዋል፤ ድርጊቶቹ ጎጂ፣ እና/ወይም ተቀባይነት የሌላቸው እንደሆኑ ተረጋግጧል፣ ነገር ግን በጥላቻ ወይም በአድልዎ ምክንያት አለመሆናቸውን ያረጋግጣል።**
- *ብርቱካን ቀለም፡-* **እውነታውን የማጣራት እርምጃዎች ተወስደዋል፤ እና ድርጊቶቹ በጥላቻ/በመድልዎ የተጠነሰሱ መሆናቸው ቢታወቅም ነገር ግን ወንጀል አይደሉም።**
- *ቀይ ምልክት፡-* ***MCPD ጋር በመተባበር እውነታውን የማጣራት እርምጃዎች ተወስደዋል። ድርጊቶቹ በጥላቻ/በመድልዎ የተከናወኑ እና ምናልባትም የወንጀል ድርጊት ሊሆኑ እንደሚችሉ ተወስኗል። ይህ ክስተት ሰፊ የሆነ ተጽዕኖ ይኖረዋል።***

### ክስተትን ሪፖርት የማድረግ ሂደት

- **ማንኛውም ሰው የጥላቻ–የመድልዎ ድርጊቶችን ሪፖርት ማድረግ ይችላል**: ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች
- ***ሪፖርት ማድረግ***: ለማንኛውም የሥራ ባልደረባ ወይም የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ መንገር ወይም በዚህ QR ኮድ ማግኘት በሚችሉት MCPS ቅጽ 226-5 ላይ ሞልተው ሪፖርት ያደርጉ።
- ለርዕሰ መምህር/ለተወካይ ያቅርቡ

ቅጽ/FORM 226-5